በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር
The Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Urban Development & Construction

754/2013

ለከተሞች መልካም አስተዳደርና አቅም ግንባታ ቢሮ
ክ/ል/ኮ/ሚ/ር

ጉዳዩ፡-**የጸደቀ መመሪያ ስለመላክ**

የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረም የኤግዚቢሽንና የከተሞች ምዝገባ መመሪያ ቁጥር 66/ 2011 ሆኖ ከጥቅምት 27 ቀን 2011 ዓ.ም ጀምሮ በሥራ ላይ እንዲውል የጸደቀ መሆኑ ይታወሳል፡፡

በመሆኑም የጸደቀው (አንድ) ጥራዝ ሰነድ ከዚህ ደብዳቤ ጋር አባሪ ተደርጎ የተላከ ስለሆነ በመመሪያው መሠረት እንዲፈጸም አስታውቃለሁ፡፡

ከሠላምታ ጋር

ጃንጥራር አባይ ይግዛው
ሚኒስትር

ግልባጭ፡

- ለክቡር ሚኒስትር ዴኤታ ( የቤቶችና መሠረተ ልማት ዘርፍ)
- ለክቡር ሚኒስትር ዴኤታ (የከተማ ልማት ዘርፍ)
- ለሚኒስትር ጽ/ቤትና ሚኒ-ካቢኔ ጉዳዮች ቢሮ
- ለሕግ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት
  ክ/ል/ኮ/ሚ/ር

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር
FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
MINISTRY OF URBAN DEVELOPMENT AND CONSTRUCTION

# የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረም የኤግዚቢሽንና የከተሞች ምዝገባ

# መመሪያ ቁጥር 754/2013

የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረም
ETHIOPIAN URBAN FORUM

ጥቅምት 2011 ዓ.ም

አዲስ አበባ፤

## መግቢያ

በኢትዮጵያ ፈጣን የከተሞች መስፋፋትን ተከትሎ የከተማ ነዋሪዎችንና የሌሎች ባለድርሻ አካላትን ተሳትፎ በማጠናከር መልካም ተሞክሮዎችንና ልምዶችን በማስፋፋት የከተማ ልማት ፖሊሲውን እና የከተማ ልማት ፕሮግራሞችን ትግበራና ስኬት ማፋጠን ይቻል ዘንድ ዓመታዊ የከተሞች ቀን፣ ሳምንትና ፎረም በመባል ተሰይሞ በተለያዩ ከተሞች አስተናጋጅነት በየዓመቱ በሀገር አቀፍ ደረጃ ሲከበር የቆየ እና ወደፊትም በየሁለት ዓመቱ የሚካሄድ በመሆኑ፣

በየሁለት ዓመቱ የሚካሄደዉ የኢትዮጵያ የከተሞች ፎረም ኤግዚቢሽን በተደራጀና ወጥ በሆነ ሁኔታ ከዝግጅት እስከ ፍፃሜ እንዲቀጥል ለማድረግ እስከ 7ኛው የከተሞች ፎረም ድረስ የተገኙ ተሞክሮዎች እና በUN-Habitat አማካኝነት የአለም የከተሞች ፎረም የኤግዚቢሽን ዝግጅት ልምዶችን በማካተት አጠቃላይ አቅጣጫ እና የትኩረት መስኮች በሚያመላክት መልኩ ተግባራዊ ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ፣

በኤግዚቢሽን ዝግጅቱ ከተሞች በዋና ዋና የከተማ አጀንዳዎች ዙሪያ በእድገት ጎዳና ለለውጥ እያደረጉት ስላለው ጥረት፣ ስላስመዘገቧቸው ስኬቶች፣ ስለገጠሟቸው ተግዳሮቶች እና ሌሎችም ተያያዥ ጉዳዮች በተሞክሮነት ሊወሰዱ የሚችሉ ስራዎቻቸውን ማራኪና በቀላሉ መልዕክት ማስተላለፍ በሚችል አቀራረብ ለህዝብ ክፍት በማድረግ መደበኛ ያልሆኑ የእርስ በርስ ውይይቶች መነሻ ነጥብ እንዲሆን በማስቻል የእውቀት ልውውጥ የሚፈጠርበት በመሆኑ፣

ይህን ለማድረግም የኤግዚቢሽን ዝግጅቱና አቀራረቡ ከዚህ በፊት ይካሄድበት ከነበረበት አካሄድ ለውጥ በማድረግ በተረጋጋ ሁኔታ መረጃ በሚሰጥና መልእክት በሚያስተላልፉ የተለያዩ ፎቶግራፎች፣ ስታንዶች፣ ዶክመንተሪዎች እና መሰል የማቅረቢያ ዘዴዎች ላይ ትኩረት ሰጥቶ መሥራት በማስፈለጉ፣ እና

የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረም ኤግዚቢሽንን በሚመለከት ለተሳታፊ ከተሞች ጠቃሚ መረጃ በመስጠት፣ የአዘጋጆችን፣ የተባባሪዎችን እንዲሁም የተሳታፊዎችን ሚና በመለየት በየሁለት ዓመቱ በሚመረጠዉ ከተማ የሚከበረውን የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረም የኤግዚቢሽን ሥራ የሚመራበትን ስርዓት ለመደንገግ ይህ መመሪያ ተዘጋጅቷል፡፡

# ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ መመሪያ የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር " የከተሞች ፎረም የኢግዚቢሽን ዝግጅትና የከተሞች ምዝገባ መመሪያ ቁጥር 754/2013 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

በዚህ መመሪያ ውስጥ:-

1) "ከተማ" ማለት ማዘጋጃ ቤት የተቋቋመበት ወይም ሁለት ሺ እና ከዚያ በላይ የህዝብ ቁጥር ያለው ሆኖ የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረም ላይ የሚሳተፍ ከተማ ወይም ተቋም ነው፡፡
2) "አዘጋጅ ከተማ" ማለት የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረም እንዲካሄድበት የተመረጠ ከተማ ነው፡፡
3) ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለጸው የሴትንም ይጨምራል፡፡

3. **የተፈጻሚነት ወሰን**

ይህ መመሪያ በየሁለት ዓመቱ ለሚካሄደዉ የከተሞች ፎረም አዘጋጆች፣ ተባባሪ አዘጋጆችና ተሳታፊ ከተሞች እንዲሁም በዝግጅቱ በሚሳተፉ ሌሎች የመንግስትና የግል ድርጅቶች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

4. **ዓላማዎች**

1) ከተሞች ከተሞች ፎረም የኢግዚቢሽን ዝግጅት ላይ እንዲሳተፉ የምዝገባ ስራ ለመፈጸም፣
2) የኤግዚቢሽን ቦታ ለማዘጋጀት፣ የሎጂስቲክና አቅርቦትን ለማመቻቸት፣
3) ደህንነቱና ጤንነቱ የተጠበቀ ኤግዚቢሽን ለመፈጸም፣ እና
4) ክልሎችና ከተሞች የራሳቸውን በዓል እንዲያከብሩ ለማገዝ የሚሉት ናቸዉ፤

5. **ከኤግዚቢሽኑ የሚጠበቁ ውጤቶች**

1) ስለ ከተሞች የልማት ሂደት እና ስለደረሱበት የዕድገት ደረጃ በነዋሪዎች እና በሌሎች ባለድርሻ አካላት ትክክለኛ ግንዛቤ ይፈጠራል፤
2) ከተሞች የልማት መስህቦቻቸውን በማስተዋወቅ ከኢንቨስትመንት፣ ከቱሪዝም፣ ከገበያ ...ወዘተ ተጠቃሚነታቸው ይጨምራል፤
3) ከተማን የማስተዋወቅ ሂደት እና ጥቅሞቹን በሚመለከት ግንዛቤ ይፈጠራል፣ ብሎም ከተሞች እራሳቸውን የማስተዋወቅ ስራ እንደ አንድ ዓብይ ተግባር ቆጥረው ልምድ እንዲወስዱ ምቹ ሁኔታ ይፈጠራል፣

4) የመረጃ ልውውጥን በማጠናከር በከተሞች እና በነዋሪዎቻቸው መሀከል ያለው መግባባት እና ትስስርና የከተማ ህዝብ ተሳትፎ ይጠናከራል፤ ንቅናቄም ይፈጠራል፤
5) በከተሞች መካከል ጤናማ ዉድድር ይፈጠራል፤

## 6. የኤግዚቢሽኑ ወቅት እና ቦታ

የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረም የኤግዚቢሽን አዘጋጅ ከተማ እና የኤግዚቢሽን የሚካሄድበት ጊዜ/ወቅት በፎረሙ ማጠቃለያ ይወሰናል፡፡

# ክፍል - ሁለት

# የተሳታፊ አካላት ተግባርና ኃላፊነት

## 7. የኤግዚቢሽኑ ተሳታፊዎች

1) ከተሞች፡- የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረም ኤግዚቢሽን ከያዘው ስፊ ከተሞችን የማስተዋወቅ ስራ እና በባለድርሻ አካላት ዘንድ ግንዛቤን የማስጨበጥ ዓላማ አኳያ ለሁሉም የኢትዮጵያ ከተሞች ክፍት ነው፡፡ የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረም ኤግዚቢሽን ከሁሉም ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች የተውጣጡ ከ200 በላይ ከተሞችና 10 ድርጅቶች እንደሚሳተፉ ይጠበቃል፡፡
2) ሌሎች ተሳታፊ ባለድርሻ አካላት፡- ከከተሞች በተጨማሪ ለከተማ ልማትና ቤቶች ዘርፉ አጋዥ የሆኑ ባለድርሻ አካላት በኤግዚቢሽኑ መሳተፍ ይችላሉ፡፡ እነዚህም፡-
   ሀ/ የክልል ከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ዘርፍ ተቋማት፤
   ለ/ አግባብነት ያላቸው የፌደራል ተቋማት፤
   ሐ/ አግባብነት ያላቸው የክልል ተቋማት፤
   መ/ የጥቃቅን እና አነስተኛ ተቋማት፤
   ሠ/ የቴክኒክና ሙያ እና የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት፤
   ረ/ የፋይናንስ ተቋማት፤
   ሰ/ አግባብነት ያላቸው የግልና የመንግስት ተቋማት፤
   ሸ/ በከተማ ጉዳዮች ዙሪያ የሚሰሩ የሲቪል ማህበራት፤
   ቀ/ አለም አቀፍ እህት ከተሞች፤
   በ/ አለም አቀፍ ድርጅቶች፤
   ተ/ በኤች. አይ. ቪ/ ኤድስ፣ በስነ ተዋልዶና ማህራዊ ጉዳይ የተሰማሩ ድርጅቶች ናቸው፡፡
3) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 2 ከፊደል ተራ ሀ-ተ የተዘረዘሩት እንደአስፈላጊነቱ የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረም አብይ ኮሚቴ በሚወስነዉ መሰረት ሊጨምር ወይም ሊቀንስ ይችላል፡፡

## 8. ዋና አዘጋጆች

የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረም ኤግዚቢሽን ዋና አዘጋጆች የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር፣ በየሁለት ዓመቱ የሚመረጠዉ አዘጋጅ ከተማ፣ የኢትዮጵያ ከተሞች የትብብር መድረክ ተባባሪ አዘጋጅ ይሆናል።

## 9. የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረም የኤግዚቢሽን ሥራ ተባባሪ አዘጋጅ

1) የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረም ኤግዚቢሽን ጥራቱን በጠበቀና የከተሞች ፎረምን ዓላማ በሚያሳካ መልኩ ማከናወን ይቻል ዘንድ በኤግዚቢሽን ዝግጅት በቂ ችሎታና ልምድ ያላቸውን ሁሉም ድርጅቶች በግልጽ ጨረታ እንዲወዳደሩ ይደረጋል፣
2) የኤግዚቢሽን ተባባሪ አዘጋጅ የሚመረጠው ግልጽ በሆነ የውድድር መስፈርት እና ሂደት ብቻ ነው፣
3) በጨረታ የተመረጠው ድርጅት የሚጠበቅበትን ተግባር በበቂ ሁኔታ መፈጸም ይኖርበታል፣ በሚወጣው መርሀ ግብር መሰረት ከሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ጋር ውል ይፈራረማል፡፡
4) አጠቃላይ ስራዎችን በተመለከተ ተባባሪ አዘጋጁ ተጠሪነቱ ለከተሞች ፎረም የቴክኒክ ኮሚቴዉም ሲሆን የኤግዚቢሽን ስራ በተመለከተ ተጠሪነቱ ለከተሞች ኤግዚቢሽን ዝግጅትና ምዝገባ ን/ኮሚቴ ይሆናል።

## 10. የከተሞች ፎረም ኤግዚቢሽንና የከተሞች ምዝገባ አስተባባሪ ንዑስ ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት፣

1) የኤግዚቢሽኑን መሪ ዕቅድ ያዘጋጃል፣ አፈጻጸሙንም ይከታተላል፣
2) የኤግዚቢሽኑን ተባባሪ አዘጋጅ የስራ ዝርዝር ቢጋር ያዘጋጃል፣
3) የኢግዚቢሽን ተባባሪ አዘጋጅ ቅጥር እንዲከናወን ያደርጋል፣ የኤግዚቢሽኑን ተባባሪ አዘጋጅ ቅጥር በእቅዱ መሰረት እንዲፈጸም የኮርፖሬትና የሃብት ስራ አመራር ቢሮና የግዥ አጽዳቂ ኮሚቴ ለስራዉ ትኩረትና ቅድሚያ ሰጥተዉ ግዥው ቀድሞ እንዲፈጸም ማድረግ ይጠበቅባቸዋል።
4) ለተሳታፊዎች ስለኤግዚቢሽኑ አጠቃላይ መረጃ በስልክና በአካል መረጃ ይሰጣል፣
5) ለኤግዚቢሽን ተሳታፊዎች የሚከራይ ከአነስተኛ እስከ ከፍተኛ ዋጋ ያለው ቦታ የዋጋ መጠን ያዘጋጃል፣ በከፈሉት የዋጋ መጠን የከተሞችን ምድብ ይወስናል፣ ቦታ በእጣ ይደለድላል፣
6) ኤግዚቢሽኑ የሚያርፍበትን ቦታ አርክቴክቸራልና ኤሌክትሪካል ፕላን በማሰራት እንዲጸድቅ ያደርጋል፣
7) የኤግዚቢሽን ተሳታፊዎች የሚፈልጉትን የቦታ መጠን እና የከተሞችን ጥያቄ መሰረት በማድረግ እና ክፍያ መክፈላቸውን በማረጋገጥ የቦታ ድልድል ይወስናል፣
8) ዘግይተው የሚመጡ ከተሞችን በመጠባበቅያነት ከተያዙት እና ለከተሞች ፎረም በዓል ዝግጅት ተመዝግበው ያልመጡ ከተሞች ድንኳኖች ክፍት መሆናቸውንና አገልግሎት አለመስጠታቸውን አረጋግጦ እንደ አመጣጥ ቅደም ተከተላቸው መስጠት እንዲቻል ለቴክኒክ ኮሚቴው የውሳኔ ሃሳብ ያቀርባል፣
9) የኤግዚቢሽን ተባባሪው በሥራ ዝርዝሩ መሠረት ተግባሩን ማከናወኑን ይከታተላል፣ የኤግዚቢሽኑን አፈጻጸምም ይከታተላል።

11. <u>በየሁለት ዓመቱ የሚመረጠዉ የከተሞች ፎረም አዘጋጅ ከተማ ተግባርና ኃላፊነት</u>

1) ለኤግዚብሽን ዝግጅት ከ10 ሄክታር ያላነሰ በቂና አመቺ ቦታ አዘጋጅቶ ያቀርባል፤
2) ለኤግዚቢሽን ቦታ አስፈላጊ የሆኑ እንደ በቂ የኤሌክትሪክ ሀይል (3 phase)፣ ኤግዚቢሽን እስከሚካሄድበት ምድረግቢ ድረስ ትራንስፎርመር ከነማከፋፈያዉ(ኤግዚቢሹኑ ከመከፈቱ አንድ ወር በፊት) እንዲተከልና መስመር እንዲዘረጋ ያደርጋል፡ የውሃ፣ የመኪና ማቆሚያ፣ የመጸዳጃ ቤቶች፣ አጥር …ወዘተ የመሳሰሉ አገልግሎቶችን ያቀርባል፣
3) የኤግዚቢሽን ተሳታፊዎች፣ ጎብኝዎችን ወዘተ…ወደ ኤግዚቢሽን ቦታ ሲመላለሱ የትራንስፖርት አገልግሎት ሊያገኙ የሚችሉበትን አሰራር ያዘረጋል፣
4) የመጀመሪያ ህክምና እርዳታ፣ አምቡላንስ እና የእሳት አደጋ መከላከያ ያቀርባል፤
5) የተጠናከረ የጥበቃ ሥራ በማከናወን የኤግዘቢሽኑን ተሳታፊዎች እና የንብረቶቻቸውን ደህንነት ያስከብራል (ፖሊስ፣ ፍ/ቤት)፣ ኤግዚቢሽን በሚሄድበት ቦታ ቁሳቁሶች የሚቀመጡበት ጊዜያዊ መጋዘን ይገነባል/ያቀርባል፣ መጀመሪያ ደረጃ የህክም መስጫ የሚያስፈልጉ የሰዉ ሃለው፣ቁሳቁስና ቦታ ያመቻቻል፡፡
6) ኤግዚቢሽኑን በከተማው ህዝብ በስፋት እንዲጎበኝ ለከተማው ነዋሪ፣ የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች አደረጃጀቶች፣ ለአንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት መምህራንና ተማሪዎች፣ እንዲሁም የዩንቨርሲቲ ማህበረሰብ ወዘተ… የቅስቀሳ ስራ ያከናውናል፣

12. <u>የከተሞች ፎረም ኤግዚቢሽን ተባባሪ አዘጋጅ ተግባርና ኃላፊነት</u>

በጨረታ ያሸነፈዉ ተባባሪ አዘጋጅ ዝርዝር ተግባርና ሃላፊነቱ በገባዉ ዉል የሚገለጽ ሲሆን የሚከተሉትን ዋና ዋና ጉዳዮች በትኩረት የሚያከናዉን ይሆናል፡፡

1) ተባባሪ አዘጋጁ በቂና ወቅታዊ ዝግጅት አድርጎ ወደ ስራ መግባት አለበት፣
2) የኢትዮጵያ ከተሞች የሚሳተፉ ከተሞችንና ድርጅቶችን እንዲመዘገቡ ያስተባባራል፤ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፡፡
3) ለኤግዚቢሽኑ ዝግጅት አስፈላጊ የሆኑ እንደ ድንኳን፣ የድንኳን ውስጥ የኤሌክትሪክ መስመር ዝርጋታ፣ ጠረጴዛና ወንበር ወዘተ የመሳሰሉ ቁሳቁሶችንና ሌሎች የኤግዚቢሽን አጋዥ መሳሪያዎችን ያቀርባል፤
4) የተሳታፊዎችን ጥያቄ ባገናዘበ መልኩ አርኪቴክቸራል ፕላን ያዘጋጃል፡፡ ይህንኑም ለንዑስ ኮሚቴው አቅርቦ ያፀድቃል፤
5) በአርኪቴክቸራል ወይም በስትራክቸራልና በኤሌክትሪካል ፕላኑ መሰረት ለሁሉም ተሳታፊ ከተሞች የድንኳን ተከላና ኤሌክትሪክ መስመር ዝርጋታ ያከናውናል፤
6) ለሁሉም ኤግዚቢሽን አቅራቢዎች በተሟላ የመብራት፣ የአምፑል፣ የአምፑል አቃፊ፣ የማብሪያና ማጥፊያ፣የብሬከር፣ ፡የገመድ፣ የሶኬት፣ የወንበር፣ የጠረጴዛ ወዘተ አቅርቦት ያላቸው የኤግዚቢሽን

ማሳያ ድንኳኖች ከሁለት ቀን በፊት ተዘጋጅቶ ለከተሞች ኤግዚቢሽን ዝግጅትና ምዝገባ ን/ኮሚቴ ይሆናል፡፡

7) ኤግዚቢሽኑ የሚካሄድብትን ቦታ የማስዋብ ስራ (በዋና ዋና በሮች ላይ ሪቫን እና ሌሎች የማስዋቢያ ቁሳቁሶችን በመጠቀም) ይሰራል፣
8) ለከተሞች ኤግዚቢሽን ዝግጅት ሙያዊ የምክር አገልግሎት ይሰጣል፤
9) ተሳታፊዎች ከኤግዚቢሽን መክፈቻ ቀን በፊት ዝግጅታቸውን እንዲያጠናቅቁ ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፤
10) ከኤግዚቢሽኑ በፊት እና በኤግዚቢሽኑ ወቅት ከተሳታፊዎች የሚነሱ (ድንኳንና ተያያዥ አገልግሎቶችን በሚመለከት) ጥያቄዎችን ያስተናግዳል፤
11) ከበዓሉ መጠናቀቅ በኋላ ለኤግዚቢሽኑ ተሳታፊዎች ንብረቶቻቸውን እንዲያነሱ አስፈላጊውን ድጋፍ ያደርጋል፤
12) ለኤግዚቢሽን ስራ የተጠቀመበትን ቁሳቁሶች ኤግዚቢሽኑ ሲጠናቀቅ ቦታን በማጽዳት ለጅግጂጋ ከተማ ንብረት ያደርጋቸዋል፡፡ ይሁን እንጂ የኤግዚቢሽን ቦታን/ምድረ ግቢውን አጽድቶ ካላስረከበ ከጠቅላላ ክፍያዉ 1% ተይዞ/ተቀርጦ ለምድረግቢዉ የጽዳት አገልግሎት እንዲዉል ይደረጋል፡፡
13) የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረም ኤግዚቢሽን በድምቀት እንዲከበር አስፈላጊውን የቴክኒክ እገዛ ያደርጋል፡፡
14) ሌሎች በውል የተሰጡትን ስራዎች ያከናውናል፡

## 13. የተሳታፊ ከተሞች፣ መ/ቤቶች፣ ድርጅቶችና ባለድርሻ አካላት ተግባርና ኃላፊነት

1) የኤግዚቢሽኑን ዓላማ ባገናዘበ መልኩ እና ይህ መመሪያ በሚያዘው መሰረት ይዘው የሚያቀርቧቸውን ዝግጅቶች ያደራጃሉ፤ ያጠናቅቃሉ፤
2) በኤግዚቢሽኑ ቦታ ቢያንስ ከሁለት ቀን በፊት ቀድመው በመገኘት ቦታቸውን ይረከባሉ፣ በተረከቡት ቦታ ላይ ብቻ ኤግዚቢሽናቸውን ይገነባሉ፤ አነስተኛ መሳሪያዎችን እንደ ፕላስተር፣ ሁክ ፕላስቲክ ገመድ፣ ሚስማር፡ ሜትር፣ የመጀመሪያ ደረጃ የሕክምና እርዳታ ወዘተ… በራሳቸው ይሸፍናሉ፡፡
3) በበዓሉ ወቅት በኤግዚቢሽኑ ቦታ በመገኘት ለጎብኝዎች መግለጫ ይሰጣሉ፣ ጥያቄዎችን ያስተናግዳሉ፤
4) ከበዓሉ ማጠቃለያ በኋላ የገነቡትን ኤግዚቢሽን እና ንብረቶቻቸውን ከአንድ ቀን ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ያነሳሉ፤
5) ኤግዚቢሽናቸውን ለመገንባት እና ለማፍረስ አስፈላጊውን የሰው ኃይል ያቀርባሉ፡፡
6) የኤግዚቢሽ ቦታና ድንኳን የከተሞች ፎረምን ዓላማ ለማሳካት ብቻ ይጠቀማሉ፤ ሆኖም የኤግዚቢሽኑን ቦታና ድንኳን የከተሞች ፎረም ካስቀመጠው ዓላማ ዉጪ መጠቀም ፈጽሞ የተከለከለ ነው፡፡
7) ከተሞች ከተረከቡት ድንኳን መጠን ዉጪ ከድንኳናቸው ፊት ለፊት ወይም በስተጀርባ ወይም በጎን አስፋፍተዉ መያዝና መጠቀም አይችሉም፡፡

## 14. የሁሉም ክልል የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ዘርፍ ተቋማት ተግባርና ኃላፊነት

1) ሁሉም የክልሉ ከተሞች በበቂ ዝግጅት እንዲሳተፉ ያስተባብራሉ፣ ያነሳሳሉ፤ ለዝግጅቶቻቸውም ድጋፍ ያደርጋሉ፤
2) የኤግዚቢሽን መመሪያውን ዋና ዋና ጉዳዮች/ጭብጦች ተሳታፊ ከተሞች በግልጽ አውቀው እንዲሳተፉ ያደርጋሉ፤
3) በከተሞች ፎረም ዝግጅት ላይ ለመሳተፍ የአቅም ውስንነት ላለባቸው የክልሉ ከተሞች ድጋፍ ያፈላልጋሉ፤ ያስተባብራሉ፤
4) ከክልሉ መገናኛ ብዙሀን ጋር በመተባበር የከተሞች ፎረም ኩነቶችን እና የከተሞችን ኤግዚቢሽን በሚመለከት መረጃ ይሰጣሉ፣ ኩነቶችን በስፋት ያስተዋውቃሉ።

## 15. የኢትዮጵያ ከተሞች ትብብር መድረክ ተግባርና ኃላፊነት

1) የከተሞች ፎረም  እንዲሳካ የቴክኒክና የፋይናንስ ድጋፍ  ያደርጋል፣
2) የኢትዮጵያ ከተሞች የሚሳተፉ ከተሞችንና ድርጅቶችን ይመዘግባል፤ አስፈላጊዉን ድጋፍ ከተሞች ምዝገባና ኤግዚቢሽን ን/ኮሚቴ  እንዲያገኝ ይደረጋል።
3) የኢትዮጵያ ከተሞች ትብብር መድረክ አባል ከተሞች የከተሞች ፎረም እንዲሳተፉ ድጋፍ ያደርጋል፣

# ክፍል ሶስት

# የኤግዚቢሽኑ ይዘት እና ጥራት

## 16. የኤግዚቢሽኑ ይዘት

1) የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረም በዋነኝነት በከተሞች፣ በነዋሪዎች እና በባለድርሻ አካላት መካከል የመረጃ እና የልምድ ልውውጥ የሚካሄድበት ስለሆነ ይዘቱም ከንግድ ወይም ከሸቀጥ ልውውጥ ኤግዚቢሽን የተለየ ሆኖ በበራሪ ወረቀቶች፣ በሞዴሎች፣ በናሙናዎች፣ በፎቶግራፎች፣ በፖስተሮች፣ በቻርቶች እና  አጭር ፊልም የሚቀርብ ይሆናል፣
2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ ከተሞችም ሆኑ ሌሎች ተሳታፊዎች በኤግዚቢሽኑ ላይ የእራሳቸውን  ምርቶች ለገበያ ማቅረብ ይችላሉ፣
3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ ከተሞች የሚያቀርቡት ኤግዚቢሽን በዋነኝነት ማንጸባርቅ ያለበት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና ቀጥሎ በአንቀጽ 17  የተገለጸውን ይሆናል፣

17. የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረምን ዓላማ ባገናዘበ መልኩ የተሳታፊ ከተሞች ኤግዚቢሽን የሚከተለው ይዘት እና ቅደም ተከተል ይኖረዋል፡፡

| ይዘት | የአቀራረብ ስልት |
|---|---|
| ጠቃላይ የከተማ መረጃ | በበራሪ ወረቀቶች፣ በሞዴሎች፣ ናሙናዎች፣ ፎቶግራፎች፣ ፖስተሮች፣ ቻርቶች አጭር ከ5 ደቂቃ ያልበለጠ ፊልም …ወዘተ የሚቀርቡ፡-<br>• ስም<br>• የህዝብ ብዛት<br>• ራዕይ<br>• ሎጎ<br>• የከተማው ልዩ መገለጫ…ወዘተ |
| ከተማ የልማታዊ አመራር ቅም ግንባታ ስራዎች | በበራሪ ወረቀቶች፣ በሞዴሎች፣ ናሙናዎች፣ ፎቶግራፎች፣ ፖስተሮች፣ ቻርቶች አጭር ከ5 ደቂቃ ያልበለጠ ፊልም … ወዘተ የሚቀርቡ፡-<br>• የለዉጥ ሰራዊት ማፍራትና ማጎልበት ሥራዎች፣<br>• የአመራርና ፈጻሚ አፈጻጸም እውቅና ግብረመልስ ሥራዎች፣<br>• የአሰራርና አደረጃጀት ዝርጋታ ሥራዎች፣<br>• የጥናት ሥራዎች፣<br>• የእቅድ አፈጻጸም ክትትል፣ ግምገማ እና ምዘና እና ትግበራ ሥራዎች፣<br>• የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂና ዳታ ቤዝ ሥራዎች፣<br>• የልማታዊ ኮሙኒኬሽን ሥራዎች |
| ከተሞች የሥራ እድል ፈጠራ ና የምግብ ዋስትና | በበራሪ ወረቀቶች፣ በሞዴሎች፣ ናሙናዎች፣ ፎቶግራፎች፣ ፖስተሮች፣ ቻርቶች አጭር ከ5 ደቂቃ ያልበለጠ ፊልም … ወዘተ የሚቀርቡ፡-<br>• የተፈጠሩ የስራ እድሎች ጠቋሚ መረጃ /ግራፎች፣ ፖስተሮች ፎቶዎች …ወዘተ<br>• የሴቶችና ወጣቶች እንዲሁም አጠቃላይ የህ/ሰቡ ተጠቃሚነት የሚያንጸባርቁ ስራዎች |
| ተሞች የልማታዊ መልካም ተዳደር ስራዎች<br>• የማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎት አሰጣጥ ስራዎች /ቂራ፣ እሳት አደጋ፣ ደረቅና ፈሳሽ ቆሻሻ ወዘተ.. /<br>• የነዋሪዎች ተሳትፎና ንቅናቄ፣ በከተሞች አገልግሎት አሰጣጥና የሰው ሀይል ልማት ላይ ያለው ተሞክሮ | በበራሪ ወረቀቶች፣ በሞዴሎች፣ ናሙናዎች፣ ፎቶግራፎች፣ ፖስተሮች፣ ቻርቶች አጭር ከ5 ደቂቃ ያልበለጠ ፊልም …ወዘተ የሚቀርቡ፡-<br>• በከተማ ልማት ዘርፎች እና በከተማ አቀፍ እንቅስቃሴዎች የኗሪዎችን ተሳትፎ ኗሪዎች የከተማውን ሰላም ለመጠበቅ የሚያደርጉት እንቅስቃሴ የሚገልፁ ፎቶግራፎችና ሌሎች ሰነዶች፣<br>• ሴቶች፣ ወጣቶች፣ የአካል ጉዳተኞች… በከተማ ልማት ያላቸው ተሳትፎ የሚያሳይ ሰነድ፣<br>• በነዋሪዎች ብቻ፣ ከግልና ከመንግስት ተቋማት ጋር የተሰሩ ስራዎች<br>• የከተማው አደረጃጀትና የሚሰጠው አገልግሎት እስከ ቀበሌ ስለመውረዱና የሰው ኃይል ስለመሟላቱ፣<br>• በከተማው አገልግሎት አሰጣጥ የህብረተሰቡ እስተያየት፣ |
| ተማ ፕላን ዝግጅት | በበራሪ ወረቀቶች፣ በሞዴሎች፣ ናሙናዎች፣ ፎቶግራፎች፣ ፖስተሮች፣ ቻርቶች አጭር ከ5 ደቂቃ ያልበለጠ ፊልም …ወዘተ የሚቀርቡ፡-<br>❖ የከተማ ፕላን<br>• መዋቅራዊ ፕላኖች፣<br>• የአካባቢዎች ፕላን ሞዴሎች፣<br>• የከተሞች ፕላን በህዝብ ተሳትፎ በመዘጋጀት ረገድ የተሰሩ ስራዎች፣<br>• የከተሞች ፕላን አፈጻጸም፣ |

| | |
|---|---|
| መሬት ልማትና ማኔጅመንት | በበራሪ ወረቀቶች፣ በሞዴሎች፣ ናሙናዎች፣ ፎቶግራፎች፣ ፖስተሮች፣ ቻርቶች አጭር ከ5 ደቂቃ ያልበለጠ ፊልም ...ወዘተ የሚቀርቡ፡-<br>• የከተማውን ግንባታና ክፍት ቦታ ለመለየት የተደረገ ጥረት፣<br>• የለማ መሬት ዝግጅት፣<br>• ለልማት የቀረበ መሬት፣(ለኢንዱስትሪና ለማኒፋክቸሪንግ፣ ለንግድ፣ ለመኖሪያ የህብረት ስራ ማህበራት፣ በመንግስት ድጋፍ ለሚከናወኑ ቤቶች፣ ለሪል ስቴት አልሚዎች ወዘተ)<br>• ያስገኘው ገቢ፣<br>• ሕገ ወጥ ግንባታ ከመከላከል ወዘተ<br>• የመሬት ዝግጅትና አቅርቦት ዋና ዋና ክንውኖች የሚገልፁ ግራፎች፣ ፎቶዎች ወዘተ...<br>• ካዳስተር የከተማ ካርታዎች ወዘተ... |
| መኖሪያ ቤቶች ልማትና ስተዳደር | በበራሪ ወረቀቶች፣ በሞዴሎች፣ ናሙናዎች፣ ፎቶግራፎች፣ ፖስተሮች፣ ቻርቶች አጭር ከ5 ደቂቃ ያልበለጠ ፊልም ...ወዘተ የሚቀርቡ፡-<br>• በመኖሪያ ቤት የህብረት ሥራ ማኅበራት የተሰሩ ቤቶች፣<br>• በመንግስት ድጋፍ የተሰሩ ቤቶች፣ ፣<br>• በግል ሪል ስቴት፣ በግል ባለሃብቶችና በግለሰብ የተሰሩ ቤቶች፣<br>• የአቅርቦት እና ፍላጎት ማመሳከሪያ ግልፅ ቻርቶች፣ ፖስተሮች ...ወዘተ<br>• የቤቶች ልማትን ተከትሎ የተፈጠሩ የስራ ዘርፎች መረጃ እና የስራ ዘርፎች ናሙና ...ወዘተ<br>• የወጣቶችና የሴቶች ተጠቃሚነት |
| ከተሞች የተቀናጀ መሰረተ ማት አቅርቦት ስራዎች ብልስቶን፣ የፍሳሽ ማስወገጃ ዎች፣ ወዘተ/ | በበራሪ ወረቀቶች፣ በሞዴሎች፣ ናሙናዎች፣ ፎቶግራፎች፣ ፖስተሮች፣ ቻርቶች አጭር ከ5 ደቂቃ ያልበለጠ ፊልም ...ወዘተ የሚቀርቡ፡-<br>• የፕሮጀክቶች ሞዴል፣ ፎቶግራፎች፣ ፖስተሮችና ቻርቶች ...ወዘተ<br>• የመሰረተ ልማት መስፋፋትን ተከትሎ የተፈጠሩ የስራ መስኮችና ሌሎች ምቹ ሁኔታዎችን የሚያሳዩ ፎቶዎች ናሙናዎች ...ወዘተ<br>• የተጠናቀቁ ፕሮጀክቶች ዓይነት እና የነዋሪው ተጠቃሚነት<br>• የከተማው የአተገባበር ስልት/ሂደት<br>• በአካባቢ መሰረተ ልማት አቅርቦት ላይ የሕ/ሰቡ ተሳትፎ |
| ከተሞች የአረንጓዴ ልማትና ፅዳት ማሻሻያ ሥራዎች | በበራሪ ወረቀቶች፣ በሞዴሎች፣ ናሙናዎች፣ ፎቶግራፎች፣ ፖስተሮች፣ ቻርቶች አጭር ከ5 ደቂቃ ያልበለጠ ፊልም ...ወዘተ የሚቀርቡ፡-<br>• ከተማዋ የከተሞች ፅዳትና አረንጓዴ ልማት ስራዎችን ለማሳካት የተፈጠረ የሕዝብ ንቅናቄ፣<br>• የከተማዋን ጽዳትና ውበት የሚያሳይ ሰነድ፣ እንደዚሁም የመንገድ ላይ፣ የአደባባይ፣ መናፈሻ ቦታዎች፣ ተቋማት...ወዘተ የአረንጓዴ ልማት ሥራዎች፣ |
| ከተሞች ገቢ(ፋይናንስ) ማትና አመራር | በበራሪ ወረቀቶች፣ በሞዴሎች፣ ናሙናዎች፣ ፎቶግራፎች፣ ፖስተሮች፣ ቻርቶች አጭር ከ5 ደቂቃ ያልበለጠ ፊልም ...ወዘተ የሚቀርቡ፡-<br>• የካፒታል ፋይናንስ አጥረትን ለመፍታት የተደረገ ጥረት<br>• የገቢ ምንጮችና አቅም በመለየት የተሰሩ ሥራዎች፣<br>• የፋይናንስ አጠቃቀም<br>• የተሰበሰበ የማዘጋጃ ቤታዊ የገቢ መጠን ጠቋሚ መረጃዎች፣<br>• በተሻሻለ የፋይናንስ ስርዓት የተገኙ ውጤቶችን የሚያሳዩ መግለጫዎች /ፎቶግራፍ ፖስተር ፊልም ወዘተ/<br>• የፋይናንስ ማኑዋሎችን የግብር ከፋዮች መረጃ<br>• ለመሰረተ ልማት፣ ለኢንዱስትሪ ማስፋፊያ እና ለሌሎች የወጣ ወጪ ወዘተ. |

| | |
|---|---|
| ስህዝብ ተደራሽና ደህንነት የሚያረጋግጥ የከተማ ልማት ሥራዎች | በበራሪ ወረቀቶች፣ በሞዴሎች፣ ናሙናዎች፣ ፎቶግራፎች፣ ፖስተሮች፣ ቻርቶች አጭር ከ5 ደቂቃ ያልበለጠ ፊልም ...ወዘተ የሚቀርቡ፡-<br>• የሴቶች ተሳታፊነትና ተጠቃሚነት<br>• የአካል ጉዳተኞች ተሳታፊነትና ተጠቃሚነት<br>• ፍትሃዊነትን ለማረጋገጥ የስራ እድል መፍጠር ስልት በመከተል የተሰሩ ስራዎች<br>• በልማት ሰራዊት አግባብ የተከናወኑ የተፋሰስ ልማት ስራ ስራዎች<br>• በከተሞች የእሳትና ድንገተኛ አደጋ መከላከያ ተቋማትን በማደራጀት የተሰሩ ስራዎች |
| ኢንቨስትመንት (ታላላቅ) | በበራሪ ወረቀቶች፣ በሞዴሎች፣ ናሙናዎች፣ ፎቶግራፎች፣ ፖስተሮች፣ ቻርቶች አጭር ከ5 ደቂቃ ያልበለጠ ፊልም ...ወዘተ የሚቀርቡ፡-<br>• የከተማዋ የኢንቨስትመንት መስህቦች፣<br>• በከተማዋ ለኢንቨስትመንት የተዘጋጁ ምቹ ሁኔታዎች፣<br>• አሁን ያለው የኢንቨስትመንት መጠን እና ዓይነት መግለጫ፣<br>• የማመልከቻ ቅፆችና ጠቃሚ አድራሻዎች፣<br>• የኢንቨስትመንት ውጤቶች (ለማስተዋወቅ ወይም ለሽያጭ የሚቀርቡ)<br>• ባለሀብቶች በከተማው ያላቸውን ኢንቨስትመንት ማስተዋወቅ |
| ቱሪዝም/ባህል | በበራሪ ወረቀቶች፣ በሞዴሎች፣ ናሙናዎች፣ ፎቶግራፎች፣ ፖስተሮች፣ ቻርቶች አጭር ከ5 ደቂቃ ያልበለጠ ፊልም ...ወዘተ የሚቀርቡ፡-<br>• የቱሪስት መስህቦች ፎቶ፣ ማስታወቂያዎች፣ ፊልሞች፣<br>• የቱሪስት መረጃዎች /በራሪ ወረቀቶች ወይም ለዚሁ ዓላማ የተዘጋጁ ጽሁፎች/፣ |
| ሌሎች | • የከተማዋን ሁኔታና ዕድገት የሚጠቁሙ መረጃዎች |

ማሳሰቢያ፡-

* የይዘት መመሪያ በዋነኝነት የሚመለከተው ከተሞችን ሲሆን ሌሎች ተሳታፊዎች የሚያቀርቡት ዝግጅት በመሰረቱ ከዚህ የተለየ ባይሆንም ከአንድ ከተማ በላይ የሚሰሩ ድርጅቶች ለብቻ በተዘጋጀ የኤግዚብሽን ቦታ ሊያቀርቡ ይችላሉ፡፡

* ኤግዚቢሽኑ በከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን የትኩረት መስኮች መሰረት መቅረብ አለበት፣ የንግድና የሽቀጣ ሸቀጥ ስራዎች ከኤግዚቢሽኑ ዓላማ ዉጪ መሆናቸዉ ከተሞች ተገንዝበዉ ዝግጅታቸዉን በከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን አምዶች (Pillars) ላይ አትኩረዉ ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡

## 18. የጥራት መመሪያዎች

1) ተሳታፊ ከተሞች የኤግዚቢሽን አቀራረባቸው ከላይ የተቀመጠውን የይዘት ቅደም ተከተል የጠበቀ መሆን አለበት፣
2) በጽሑፍ የሚቀርቡ መረጃዎች በግልጽ የሚነበቡ እና ግድፈት የሌለባቸው መሆን አለባቸው፣ በተጨማሪም በእጅ ያልተጻፉ (በኮምፒዉተር የተጻፉ) እና ባለቀለም መሆን አለባቸዉ፣
3) የመረጃ ቻርቶች ባለቀለም፣ በግልጽ የሚታዩ፣ በእጅ ያልተዘጋጁ መሆን ይኖርባቸዋል፣ በሚታይ ሁኔታም መሰቀል አለባቸው፣ የቻርቶቹ መጠን ከA3 መጠን ያላነሰ መሆን አለበት፣

4) የመረጃ ዶክሜንተሪ ፊልሞች ርዝመት ከ5 ደቂቃ በላይ መሆን የለባቸውም፤
5) ፎቶ ግራፎች በጥራት የተነሱ ገላጭ እና ለጎብኝዎች ወይም ለእይታ አመቺ መጠን ያላቸው መሆን ይገባቸዋል፣
6) ለኤግዚቢሽን የሚቀርቡ የፎቶ ግራፎች መጠን ከA4 መጠን ያላነሰ መሆን አለበት፤
7) ተሳታፊ ከተሞች ከኤግዚቢሽናቸው ይዘት በተጨማሪ ጥራት ላለው አቀራረብ በርትተው መስራት ይጠበቅባቸዋል፡፡
8) የኤግዚቢሽኑ ዝቅተኛ የጥራት መስፈርቶች በዋነኝነት የሚመለከተው ከተሞችን ሲሆን ሌሎች ተሳታፊዎች የሚያቀርቡት ዝግጅት ለፎረሙ የሚመጥን መሆን አለበት፡፡

19. ለጎብኚዎች የሚደረግ ገለጻ

1) ተሳታፊ ከተሞች ከኤግዚቢሽኑ መክፈቻ እስከ መዝጊያው ድረስ ለእንግዶች ተገቢውን ገለጻ የሚያደርጉ ባለሞያዎችን መመደብ ይጠበቅባቸዋል፣
2) ገለጻ ሰጪዎች በኤግዚቢሽን ዝግጅት ላይ ገለጻ የማድረግ ልምድ ሊኖራቸው ይገባል፣
3) በመክፈቻው ቀን ለሚጎበኙ የክብር እንግዶች የሚሰጥ ገለጻ ለ5 ደቂቃ ያህል ይሆናል፡፡

## ክፍል - አራት

## የኤግዚቢሽን ቦታ አሰጣጥ፣ አጠቃቀም እና የተሳትፎ ክፍያ

20. የኤግዚቢሽን ቦታ አሰጣጥ እና አጠቃቀም

1) አንድ ተሳታፊ የሚሰጠው አነስተኛ የቦታ መጠን 12 ካሬ ሜትር ሲሆን ከፍተኛው ከ600 ካሬ ሜትር መብለጥ የሌለበት ሆኖ በአንቀጽ 20 ንኡስ አንቀጾች 1፣ 2 እና 3 መሰረት በከተሞች ፍላጎት የሚወሰን ይሆናል፤
2) ምዝገባ የሚከናወነዉ መዘጋቢዉ አካል ወይም ኤግዚቢሽን ዝግጅትና የከተሞች ምዝገባ ንዑስ ኮሚቴ ከተሞች በባንክ የከፈሉበት ደረሰኝ ሲደርሰዉ ይሆናል፡፡
3) የኤግዚቢሽን ቦታ ድልድል የሚካሄደው ተሳታፊ ከተሞች በሚያቀርቡት የቦታ ጥያቄ መሰረት ሆኖ በኤግዚቢሽን ንዑስ ኮሚቴ አማካኝነት የሚከናወን ይሆናል፡፡ ይህም በሚከተለው ሂደት ይከናወናል፡-

ሀ/ ተሳታፊ ከተሞች የሚፈልጉትን የቦታ መጠን ኤግዚቢሽኑ መክፈቻ እለት 30 ቀናት ቀድመው ያሳውቃሉ፣

ለ/ ተሳታፊዎች ለሚፈልጉት ቦታ የሚጠበቀውን ኤግዚቢሽኑ መክፈቻ እለት 25 ቀናት ቀድመው ያሳውቃሉ፣

ሐ/ ተሳታፊዎች የሚጠይቁት የቦታ መጠን ከሚፈቀደው ከፍተኛ የቦታ መጠን በላይ ከሆነ እንደ አስፈላጊነቱ በኤግዚቢሽን ንዑስ ኮሚቴ ውሳኔ ተሰጥቶበት አስፈላጊውን ክፍያ እንዲፈፅሙ ተደርጐ ሊሰጣቸው ይችላል፤

መ/ ማንኛውም ተሳታፊ በኤግዚቢሽኑ ቦታ የተዘጋጀለትን ቦታ ለመረከብ ሲቀርብ የክፍያ ማረጋገጫ ደረሰኝ ወይም የባንክ የገንዘብ ትራንስፈር ማስረጃ ማቅረብ አለበት፤

ሠ/ ለተሳታፊዎች የሚሰጠው ቦታ በእጣ የሚወሰን ሆኖ ትላልቅና ትናንሽ ከተሞችን በማቀላቀል ይደለደላል፤

ረ/ የኤግዚቢሽን ቦታ አሰጣጥ (የኤግዚቢሽን ምዝገባና ቦታ የመደልደል ሥራ) በከተሞች ፎረም የኢግዚቢሽን ዝግጅትና የከተሞች ምዝገባ ንኡስ ኮሚቴ ይከናወናል፣

4) የኤግዚቢሽኑ ተሳታፊዎች ከኤግዚቢሽኑ መክፈቻ 2 ቀን በፊት ቦታቸውን ይረከባሉ፣

5) የኢግዚቢሽኑ ተሳታፊዎች ኤግዚቢሽኑ ከሚከፈትበት ቀን ዋዜማ የዲስፕሌይ ዝግጅቶቻቸውን ማጠናቀቅ አለባቸው፡፡ በኤግዚቢሽኑ መክፈቻ ወቅት ማንኛውንም የግንባታ እና የዲስፕሌይ ዝግጅት ማከናወን በጥብቅ የተከለከለ ነው፤

6) የኤግዚቢሽኑ ቦታ በየዕለቱ ከጠዋቱ 1፡00 ሰዓት ጀምሮ እስከ ምሽቱ 2፡00 ሰዓት ድረስ ለተሳታፊዎች እና ጎብኚዎች ክፍት ይሆናል፤

7) የወሰዱትን ድንኳን ወይም ቦታ ለሦስተኛ ወገን ሙሉ በሙሉ አሳልፎ መስጠት የተከለከለ ነው፤ ያለአግባብ ሲጠቀም የተገኘ ሶስተኛ ወገን እንዲለቅ ይደረጋል፤ ቦታውን አሳልፎ ለሶስተኛ ወገን በሰጠ አካልም አስተዳደራዊ እርምጃ ይወሰድበታል፤

8) የተሳታፊዎችን ንብረት ደህንነት ለመጠበቅ እንዲያመች ከምሽቱ 2፡00 ሰዓት እስከ ጠዋቱ 1፡00 ሰዓት በኤግዚቢሽኑ ቦታ ከጥበቃ አባላት በስተቀር ማንም እንዲገኝ አይፈቀድም፡፡

21. <u>የተሳትፎ ክፍያ</u>

1) በኤግዚቢሽኑ ለመሳተፍ፡፡

ሀ/ የምዝገባ ክፍያ

- ለመጀመሪያዉ ዙር የULGDP 19 ተጠቃሚ ከተሞች ብር 2,500.00
- ለሁለተኛዉ ዙር የULGDP 26 ተጠቃሚ ከተሞች ብር 2,000.00
- ለሌሎች ከተሞች ብር 1,500.00

ለ/ ለሁሉም ከተሞች የቦታ ኪራይ ለአንድ ቀን በካሬ ሜትር ብር 250.00 መክፈል ይጠበቅባቸዋል፡፡

2) ተሳታፊዎች የኤግዚቢሽን ቦታውን የሚከራዩት ለ7 ቀን ብቻ ነው፤ ተሳታፊዎች የሚጠይቁት የቦታ መጠን ቀጥሎ በሰንጠረዥ ከተመለከተው ከ12 እስከ 600 ካሬ ሜትር ብቻ ይሆናል፤ ልዩ ሁኔታዎች ሲገጥሙ በልዩ ሁኔታ እንዲስተናገዱ ይደረጋል፡፡ ከተሞች በጠየቁት የቦታ መጠን ልክ ቦታ ማግኘት አለባቸው፣ ከዲዛይን ውጪ የቦታ ማሽጋሸግ አይቻልም፣

3) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ የተገለጸዉ ክፍያ እንደ ወቅቱ ሁኔታ ሊጨምር ይችላል፡

| ተ.ቁ | የሚቀርቡ ቁሳቁሶችና አገልግሎቶች ዝርዝር | መግለጫ | መለኪያ |
|---|---|---|---|
| 1) | ድንኳን፣ ጠረጴዛና ወንበር | 600 ካሬ ሜትር (30X20) | በቁጥር |
| 2) | ድንኳን፣ ጠረጴዛና ወንበር | 500 ካሬ ሜትር (25X20) | በቁጥር |
| 3) | ድንኳን፣ ጠረጴዛና ወንበር | 400 ካሬ ሜትር (20X20) | በቁጥር |
| 4) | ድንኳን፣ ጠረጴዛና ወንበር | 300 ካሬ ሜትር (15X20) | በቁጥር |
| 5) | ድንኳን፣ ጠረጴዛና ወንበር | 200 ካሬ ሜትር (10X20) | በቁጥር |
| 6) | ድንኳን፣ ጠረጴዛና ወንበር | 150 ካሬ ሜትር (10X15) | በቁጥር |
| 7) | ድንኳን፣ ጠረጴዛና ወንበር | 100 ካሬ ሜትር (10X10) | በቁጥር |
| 8) | ድንኳን፣ ጠረጴዛና ወንበር | 80 ካሬ ሜትር (10X8) | በቁጥር |
| 9) | ድንኳን፣ ጠረጴዛና ወንበር | 60 ካሬ ሜትር (10X6) | በቁጥር |
| 10) | ድንኳን፣ ጠረጴዛና ወንበር | 40 ካሬ ሜትር (8X5) | በቁጥር |
| 11) | ድንኳን፣ ጠረጴዛና ወንበር | 20 ካሬ ሜትር (5X4) | በቁጥር |
| 12) | ድንኳን፣ ጠረጴዛና ወንበር | 16 ካሬ ሜትር (4X4) | በቁጥር |
| 13) | ድንኳን፣ ጠረጴዛና ወንበር | 12 ካሬ ሜትር (4X3) | በቁጥር |

4) ከዚህ በታች የተዘረዘሩት አካላት የቦታ ክፍያ አይመለከታቸውም፡-

ሀ/ ከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴርና ተጠሪ ተቋማት፣

ለ/ የኤች. አይ. ቪ. ግንዛቤ ማስጨበጫና የበጎ ፈቃደኝነት ምርመራ፤

ሐ/ ያለክፍያ ተመጣጣኝ የድንኳን መጠን የሚሰጣቸው ድርጅቶች፣ መስሪያ ቤቶችና ተቋማት /ቀይ መስቀል፣ እሳት አደጋ፣ የጤና ተቋማት፣ የጸጥታና የትራንስፖርት ደህንነት አካላት፣ ወዘተ/ ካለው ቦታ አንጻር ታይቶ የከተሞች ፎረም ቴክኒክ ኮሚቴ ሊወሰን ይችላል፡፡ ጅግጅጋ ከተማ አዘጋጅ ከተማ በመሆኗ 600 ካሬ ሜትር በነጻ የሚሰጣት ሲሆን ከ600 ካሬ ሜትር በላይ ከጠየቀች ለተጨማሪው የቦታ መጠን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ፊደል ተራ (ለ) በተቀመጠው የኪራይ ዋጋ መሰረት የምትስተናገድ ሆኖ የቦታ ምርጫዋም ይጠበቅላታል፡፡

መ/ የተሳታፊ ከተሞች በተያዘዉ የጊዜ ገደብ በኋላ ክፍያ የፈጸሙ ከሆነ ከእጣ ዉጪ እንዲሆኑ ተደርጎ ቀድመው የተመዘገቡ ከተሞች በእጣ ከደረሳቸዉ ድንኳኖች ዉጪ ያሉትን ቦታዎች እንዲያገኙ ያደርጋል፡፡

ሠ/ የምዝገባ እና የድንኳን/የቦታ ኪራይ በከተማች ስም መፈፀም አለበት፡፡ ይሁን እንጂ በግለሰብ ስም ክፍያዉ ተፈጽሞ ቢገኝ ለሚደርሰዉ ችግር ከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ተጠያቂ አይሆንም፡፡

ረ/ ከተሞች ክፍያ ከፈጸሙበት የድንኳን መጠን አንሶ ሲገኝ ባልተጠቀሙበት የድንኳን መጠን ልክ ተሰልቶ እንዲመለስላቸዉ ይደረጋል፡፡

## 22. የድምጽ አጠቃቀም

1) ኤግዚቢሽኑን ብሎም ሌሎች የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረም ዝግጅቶችን በተሳካ ሁኔታ ለማከናወን ይቻል ዘንድ የበዓሉ ቦታ ለመደማመጥና መግለጫዎችን በተገቢው ሁኔታ ለመስጠት ምቹ መሆን አለበት፤
2) ተሳታፊዎች የሚጠቀሙባቸው እንደ ሙዚቃ፣ የቴሌቪዥን ማስታወቂያዎች፣ ፊልሞች፣ መግለጫዎች፣ ወዘተ የመሳሰሉት ድምፅ የሚያወጡ ግብዓቶች ከተሞች በሚወጣለቸው ፕሮግራም መሰረት መሆን አለበት፤ ካልተቻለም በአካባቢያቸው ያሉትን ሌሎች ተሳታፊዎች በማያውክ ሁኔታ መጠቀም ይጠበቅባቸዋል፤
3) ከተሳታፊ ከተሞች የሚለቀቀው የሙዚቃ ድምጽ መጠን ከ 80 dB መብለጥ የለበትም፡፡
4) የድንጽ ማጉያ ወይም የሙዚቃ መሳሪያ በመጠቀምም ሆነ በሌላ መንገድ ሙዚቃ ማሰማት የሚቻለው ከቀኑ 6:00 ሰዓት እስከ 8:00 ሰዓት ድረስ ባለው ጊዜ ብቻ ነው፤ ከዚህ ጊዜ ውጭ ሙዚቃ ማሰማት አጥብቆ የተከለከለ ነው፡፡
5) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) ከተገለጸው መጠን በላይ የሆነ እና አካባቢን የሚያውኩ ድምጾችን የሚያመነጭ ተሳታፊ ከተማ ወይም ከተፈቀደው ሰዓት ውጭ ሙዚቃ የሚያሰማ ተሳታፊ ከተማ ሆኖ ከተገኘ ከተሞችን ለሚያወዳድሩ እስከ 15 በመቶ ከተማዉ ከሚያገኘዉ ነጥብ እንዲቀነስ ለዉድድር ኮሚቴ መረጃዉ እንዲላክ ይደረጋል፡፡
   ሀ) ለመጀመሪያ ጥፋት/መተላለፍ የቃል ማስጠንቀቂያ ያስጠዋል፣
   ለ) ለሁለተኛው ጥፋት/መተላለፍ አጠቃላይ ከተማው ከሚያገኘው ነጥብ 15 በመቶ እንዲቀነስ ይደረጋል፣
   ሐ) ለሶስተኛው ጥፋት/መተላለፍ የድምጽ ማጉያ መሳሪያዎሪያውን እስከ ኤግዚቢሽኑ ፍጻሜ ድረስ እንዲያስረክብ ይደረጋል፡፡

## 23. የጊዜ ሰሌዳ

የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረም የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር በየሁለት ዓመቱ በሚወስነዉ የጊዜ ሰሌዳ መሠረት የሚካሄድ ይሆናል፡፡

## ክፍል - አምስት
## የኤግዚቢሽን ዝግጅት ወጪዎች እና የበጀት ምንጭ

### 24. የኤግዚቢሽን ዝግጅት ወጪዎች

የኤግዚቢሽን ዝግጅት ወጪዎች የሚባሉት የሚከተሉት ናቸው፡-

1) የቦታ ዝግጅት ወጪዎች (የቦታ ድልደላን፣ የአጥር ግንባታን፣ የመብራት እና የውሃ መስመር ዝርጋታን ለማከናወን የወጡ ወጪዎች)
2) የድንኳን ኪራይ፣
3) የአርክቴክቸራል እና ኤሌክትሪካል ፕላን፣
4) የኤሌክትሪክ መስመር ዝርጋታ፣ የድንኳን ተከላ እና ማፍረሻ
5) አስፈላጊ የኤግዚቢሽን ቁሳቁሶች (ወንበር፣ ጠረጴዛ፣ የኤሌክትሪክ ገመድ፣ መደሻ ወዘተ… የመሳሰሉት) ኪራይና ግዥ ወጪዎች ናቸው።

### 25. የኤግዚቢሽን ዝግጅት የበጀት ምንጭ

የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረም ኤግዚቢሽን ወጪዎች የበጀት ምንጭ በየሁለት ዓመቱ በሚመረጠዉ አዘጋጅ ከተማ፣ ከተሳታፊ ከተሞች የተሳትፎ ክፍያ እና ለኤግዚቢሽን ዝግጅቱ ከአዘጋጆችና ከስፖንሰሮች የሚሰበሰበው ገንዘብ ነው።

## ክፍል - ስድስት
## ስለኤግዚቢሽኑ መረጃ ስለማግኘት

### 26. ኤግዚቢሽንን በሚመለከት መረጃ ስለማግኘት

1) የከተሞች ፎረም የኤግዚቢሽን መረጃ በየሁለት ዓመቱ በሚዘጋጅዉ የከተሞች ፎረም መሪ እቅድ ዉስጥ ተካቶ ለክልሎችና ለከተሞች እንዲሰራጭና እንዲያዉቁት ይደረጋል ፣
2) መረጃዎች በሚኒስትር መስሪያ ቤቱ ዌብ ሳይት እንዲጫን ይደረጋል።

### 27. ኃላፊነቱን በማይወጣ አካል ላይ ስለሚወሰድ እርምጃና ቅጣት

1) ተባባሪ አዘጋጁ የኤግዚቢሽን ድንኳን ተከላ እና የኤሌክትሪክ መስመር ዝርጋታ ሥራን የከተሞች ፎረም በዓል ከሚጀመርበት ሁለት ቀናት ቀድሞ ካላስረከበ ለጠቅላላ ድንኳኖች ከሚከፈለው ጥቅል ክፍያ ላይ 10 በመቶ ተቀንሶ ለመ/ቤቱ ገቢ ይሆናል።
2) የዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 እንደተጠበቀ ሆኖ ተባባሪ አዘጋጁ ግንባታ ለመፈጸም በተቀመጠው መርሐ-ግብር መሰረት ኤግዚቢሽን በሚካሄድበት ቦታ ላይ ኤግዚቢሽኑ ከመካሄዱ ሁለት ቀን በፊት

ተገኝቶ ግንባታውን በሙሉ ካላከናወነ መ/ቤቱ አስፈላጊውን አማራጭ የሚወስድ ሆኖ ለሚፈጠረው ኪሳራ ተባባሪ አዘጋጁ ኃላፊነት አለበት፡፡

3) ተባባሪ አዘጋጁ ኤግዚቢሽኑ ከተጠናቀቀ በኋላ ለዝግጅቱ ያቀረባቸውን ቁሳቁሶች በማንሳት የኤግዚቢሽን ቦታውን በሁለት ቀናት ውስጥ አጽድቶ ማስረከብ አለበት፣ ይሁን እንጅ የኤግዚቢሽን ቦታን/ምድረ ግቢውን አጽድቶ ካላስረከበ ከጠቅላላ ክፍያዉ 1% ተይዞ/ተቆርጦ ለምድረግቢዉ የጽዳት አገልግሎት እንዲዉል ይደረጋል፡፡

## 28. መመሪያውን ስለማሻሻል

ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ይህንን መመሪያ ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘዉ ሊያሻሽለው ይችላል፡፡

## 29. የተሻሩ መመሪያዎች

የ7ኛው የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረም የኤግዚቢሽን ዝግጅት መመሪያ ቁጥር 57/2009 በዚህ መመሪያ ተሽሯል፡፡

## 30. መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከጥቅምት 27 ቀን 2011 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

ጃንጥራር አባይ ይግዛው
ሚኒስትር

The Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Urban Development & Construction

የኢፌዲሪ ከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ሚኒስትር

## አባሪ 1፡ ኤግዚቢሽንን በተመለከተ መረጃ ማግኘት የሚቻለዉ

1) የከተሞች ፎረም የኤግዚቢሽን ምዝገባ በተመለከተ የአስተባባሪዎች በሞባይል ቁጥር 0912140105 ወይም 0934480214 ወይም 0911169001 በመደወል መረጃ ማግኘት ይችላሉ፤
2) ተሳታፊዎች የኤግዚቢሽን ቦታ ጥያቄ፣ የምዝገባና ክፍያን የሚመለከቱ መረጃዎች በስልክ ቁጥር 0115576055 በሞባይል ቁጥር 0910173789 ወይም 0911169001 ወይም በመደወል ማግኘት ይቻላል፤
3) ተሳታፊዎች ለመመዝገቢያ እና ለቦታ የሚከፍሉትን ክፍያ "በከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር- የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረም" "Ministry of Urban Development & Construction — Ethiopian Urban Forum" የባንክ ሂሳብ ቁጥር 1000191468655 የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ አዲስ አበባ ቅርንጫፍ ገቢ በማድረግ በከተማው ስም ገቢ የተደረገበት ማስረጃ በፋክስ ቁጥር 0115576088 ወይም 0115541268 ለ8ኛው የከተሞች ፎረም ተብሎ ኮፒው መላክ ይኖርበታል።

## አባሪ 2. የኤግዚቢሽን ዝግጅት ዋና ዋና ተግባራት በሚከተለዉ የጊዜ ሰሌዳ መሰረት ይከናወናል

| .ቁ | ተግባር | ቀን |
|---|---|---|
| | የአውደ ርዕይ ተሳትፎ ምዝገባና የቦታ መጠን ጥያቄ ማቅረብ | እስከ ታህሳስ 07 01/2011 |
| | የቦታ እና የምዝገባ ክፍያ ማጠናቀቅ | እስከ ጥር 07 /2011 |
| | የኢግዚቢሽን ቦታ ዝግጅት፣ የመብራት እና ውሃ አቅርቦት፣ የአጥር ግንባታ፣ የመጸዳጃ ቤቶች ግንባታ፣ የቆሻሻ መጣያ ቦታዎች ዝግጅት ወዘተ. ማጠናቀቂያ | እስከ ጥር 23 /2011 |
| | የኢግዚቢሽን ግንባታ ማጠናቀቂያ | እስከ የካቲት 04/2011 |
| | የድንኳን ተከላና ማስዋብ እና የኤሌክትሪክ መስመር ዝርጋታ ማጠናቀቅ | እስከ የካቲት 5/2011 (ከኢግዚቢሽን መክፈቻ ከ2 ቀናት በፊት) |
| | የኢግዚቢሽን ቦታ ርክክብ | እስከ የካቲት 5/2011<br>ጠዋት 2፡ 30 ሰዓት |
| | የኢግዚቢሽን መክፈቻ | የካቲት 7/2011 |
| | የአውደ ርዕይ ማጠናቀቂያ | የካቲት 13/2011 |
| | የአውደ ርዕይ ቁሳቁስ ማንሻ | የካቲት 13 - 14/2011 |